## ምድብ ሦስት (ከ4ኛ — 6ኛ) ክፍል

## 8 ኛ ሳምንት

# ያዕቆብ እና ዔሳው

### ዓላማ

- ስለ ወንድማማቾቹ ያዕቆብ እና ዔሳው ታሪክ ማወቅ እና የበረከትን ጥቅም መማር፡፡

### በቃል የሚጠና ጥቅስ

- «ቆይቼ እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት÷እርሱም ዘንበል አለልኝ ጩኸቴንም ሰማኝ፡፡» መዝ.39(40)÷1

### ምንባባት

- ዘፍጥ.25÷32÷24-29

### መግቢያ

- ይስሐቅና ርብቃ የአብርሃምን መንገድ ተከትለው እግዚአብሔርን በመፍራትና በመከተል ኖረው ልጆች ወለዱ፡፡
- ይስሐቅም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበር በረከት የመስጠት ሀብት ነበረው፡፡
- ልጆቹ ሊባረኩ ያደረጉትን ጥረት በቀጣዮ ትምህርት እናያለን፡፡

### የትምህርቱ ይዘት፣

- ርብቃና ይስሀቅ ልጆች ሳይኖራቸው ለረጅም ጊዜ ኖረዋል፡፡ይስሀቅ ፀለየ ልጅም አገኙ፣ ልጆቹም መንትያ ነበሩ፡፡ የመጀመሪያው ዔሳው ሁለተኛውም ያዕቆብ ነበር ስማቸው፡፡
- ልጆቹም አደጉ ዔሳው አዳኝ ሲሆን፣ ያዕቆብም በድንኳን ውስጥ እናቱን ይረዳ ነበር፡፡
- አንድ ቀን ዔሳው በጣም ተርቦ ከአደን ተመለሰ ያዕቆብ ወጥ ሲሰራ አየቶ አብላኝ አለው፣ ብኩርናህን ሽጥልኝ እና አበላሃለው አለ፡፡
- ልጆች ብኩርና ምንድ ነው? የመጀመሪያ ልጅ የሚያገኘው ስጦታ፣ሲሆን ከአባቱም በረከት ያስገኝለት ነበር፡፡ ኤሳው እና ያዕቆብም መንትዮች ነበሩ፡፡ ኤሳው መጀመሪያ ስለወጣም ብኩርናው የእርሱ ነበር፡፡
- ያዕቆብ ብኩርናውን እንዲሸጥለት ሲጠይቀው ግን ***«እኔ ልሞት ነኝ(በረሃብ) ይህቺ ብኩርና ለምኔ ናት?»*** ብሎ ማለለት እና ሸጠለት፡፡ያዕቆብም ዳቦ እና ምሥር ወጥ ሠጠው፡፡ ዔሳው በላ እና በመንገዱ ሄደ፡፡
- ዔሳው ብኩርናውን ናቃት ስለ ምግብም ለያዕቆብ ሸጣት፡፡
- ይስሐቅ አረጀ፣ ያዕቆብም የአባቱን በረከት አገኘ፤ ዔሳው ግን አላገኘም በኂላ ቢፈልገውም አላገኘውም፡፡ በጣም ተበሳጨም፡፡
- ያዕቆብ የአባቶችን እና የእግዚአብሔርን በረከት ያውቃል፡፡ ስለዚህም የአባቱን በረከት ተቀበለ፡፡ በኂላም ያዕቆብ የእግዚአብሔርን በረከት ለማግኘት ታገለ እግዘአብሔርም ባረከው ስሙንም ***እስራኤል*** አለው፡፡

### ጥያቄዎች

1. የይስሐቅና የርብቃ መንትያ ልጆች ማን ይባላሉ?
2. መጀመሪያ የተወለደው ማነው?
3. የብኩርና ልዩ ስጦታ ምንድነው?
4. የብኩርናን በረከት የወሰደው ማነው?
5. ዔሳው ስለብኩርናው የሚያስበው ምን ነበር?
6. ከቤተሰቦቻችሁ፣ ከአያቶቻችሁ? ከቤተክርስቲያን ካህናትም በረከትን ትቀበላላችሁ? በቤተሰባችሁ ለመባረክ ትጥራላችሁ? ምሳሌ ስጡ፡፡

**ይቆየን፡፡**